ባለጌ እውነት

"ዛሬ አንቺን እንዲህ እንደሚያደርግሽ እኔንም እንዲሁ ያደርገኝ ነበር፤ አልፈንበት ነው እቱ ዝም ያልነው እንጂሳናውቅ ቀርተን እንዳይመስልሽ...ተወደድኩ ብለሽ አትበይ ደንበር ደንበር እኛንም አንጊዜ እነዲህ አድርጎን ነበር" ...በእድሜ ተኮንነው ያጡትን የወጣትነት ዘመን ውበትና ቁንጅና ንቀውት እንዳለፉ ሁሉ ትተነው ነው እያሉ የሚያወሯት ነገር አይገባትም ...በወጤነታቸው ዘመን የለየላቸው አለሌ እንደሆኑ ሰፈሩ ምስክር ነው...ዛሬ ምንም ዋጋ የለው የሚሉትን ሁሉ ለማጣጣም ሲሉ የእድሜአቸውን እኩሌታ አባክነዋል..."ከአንዱ ወደአንዱ መንዛለል ቁም ነገር አይምሰልሽ" ካሉ ከአንዱ ወደአንዱ ይዛለሉ ነበር ማለት ነው። የእድሜ ፍርሃት ጭነት ያመጣባቸው ጉብጠት ተንጠራርቶ ከወጣትነት ፍሬ ለመቀንጠፍ ስለከለከላቸው ይሆን ወይ ደግሞ ያሳለፉት ህይወት መናነቱን በእድሜ መዝነው አይተው እንደሁ ከንቱ ነው የሚሉት ግልጽ አይደለም...

"ሰለሞን እንኳ ስንቱን ካሸሞነሞነ በኋላ ሁሉ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ነው ያለው"

"ሰለሞን እኮ ብዙ ዓመት ኖሯል፤በዛ ላይ እንደው እውነቱን ለመናገር እሱ ያየውን እንደው ማየቱ ይቅርና አስበነው እራሱ መች እናውቃለን...ደግሞ እኮ ለሰለሞን የደበረው ነገር ለሌላውም እኮ ያስጠላዋል ማለት አይደለም"

"ለሰለሞን ጊዜ ሲሆን አፍሽን ታሞጠመጫለሽ እንግዲህ ኖሮ ያየ ሰው አይበጅም ካለ መቀበል ነው እንጂ ኖሬ ካላየሁ አላምንም ማለት የህጻን ልጅ ድርጊት ነው፤ የዘመኑ ወጣት ሲነገራችሁ አትሰሙ ሁሉን ካላየሁ ማለት"

"እሺ እሱን ተይው እና አንድ ነገር እኮ እድሜው በገፋ ቁጥር ያረጅና በሌላ ነገር ይተካል ለእውነትም እነደዚሁ ነው የአንድ ዘመን እውነት እውነታነቱ ለዘመኑ ብቻ ነው" አቋርጠዋት ይገባሉ

"እና እውነትሽን አስረጂኛ እስኪ፤እናም የእኔን እውነታ ውሸት መሆኑንም አሳዪኝ"

"አታምኚኝማ" እጇን ከአናቷ በላይ እያወረጨች፤ ስትበሳጭ እንዲህ ደርጋታል

"ድሮንስ ላምንሽ ፈልገሽ ነበር"

"ካላመንሽኝ ታድያ ለምን አስረዳሻለው?"

"እንጃባሽ ቆይ ቀድሞ ነገር ቢቀርብሽስ፤የምን መሚዘዝ ነው እቱ ያንቺ ደግሞ ልክ አጣ ማርም ሲበዛ እኮ ይመራል" ማሩን በልተው መረራቸው ያህል ፊታቸው ቀጨመ

"እሺ አንቺ ማር እስኪመርሽ ድረስ በልተሽ ታውቂያለሽ?" የተንኮል ፈገግታ ፊቷ ላይ አለ

"ቀድሞ ነገር ማር የሚባል ነገር በልጅነቴ ማር ውስጥ ንብ ሞታ ካየሁ ወዲህ እንደማልወድ ታውቂያለሽ አይደል እንዴ...

"እኮ ታድያ ማሩን ሳትበይ ስለማሩ መምረር እንዴት ልታውቂ ቻልሽ?" ተንኮሏ ግቡን እንደመታ ተሰማት መሰል

"ከአባባሉ ከሆነ ችግርሽ እንግዲህ ልቀይርልሻ...እም..." ከአፋቸው የሚወጣውን ሃሳብ ባርኮት እንደሚቀበል ሰው በጉጉት ትጠባበቃለች...ሃሳቡን ከጣርያ ያወርዱት ይመስል ጣርያው ላይ አፍጥጠውበት ቆዩ፤ጣርያው ሳይገጅር አልቀረም መሰል ተስፋ ቆርጠው ወለሉን በአይናቸው ዳበሱት፤ ምናልባት ከጣርያው የወደቀ ሃሳብ እየፈለጉ ይሆናል...መሬት ደግ አይደለችም የፈለጉትን ሃሳብ ሳይሆን የፈለገቸውን ሃሳብ ሰጠቻቸው...ያቺ ልኬለሽ የቤት ኪራዩን ገንዘብ አዘግይታ መስጠቷ ሳያንስ ሙሉውን መክፈል አልችልም ብላ በእንባ የታጀበ ጎዶሎ ብር ነው የሰጠቻቸው፤ለቀጣይ ወርም ማገኘቷን እንጃ...ተከራይ ሆኖ በየወሩ የአከራይን ካዝና ለጣርያቸውና ለግድግዳቸው ቸርነት ሲሉ መመላትን ያውቁታል ታድያ በእሳቸው የሆነውን በሌላ ላለመድገም ሲሉ ለተከራይ የማያሳዩት ቸርነት አልነበረም የቤት ኪራይን ከመተው አልፎም የወር አስቤዛን እስከማካፈል...የልኬለሽ ግን ልክ አጣ ለጣርያውና ለግድግዳው ባትከፍል መብራቱና ውሃው በነጻ አልመጣ ታድያ ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው የሞላኑሮ እየኖሩ ወር በደረሰ ቁጥር ለቤት ኪራይ ማለቃቀስ...ጎዶሎ ብሩን ሲቀበሉ በኃይለ ቃል ተናግረዋታል...እናም ፈጣሪ ቸርነት አድርጎ ዛሬ አከራይ ቢያደርጋቸው ተከራይ ላይ እንዱህ መሆናቸው ፈጣሪን ያስከፋ ድርጊት የፈጸሙ፤ ፈጣሪም በዚህ ተናዶ በተዓምራቱ ከኪራይ ቤት እንዳወጣ በተአምራቱ ወደኪራይ ቤት እንዳይመልሳቸው ሰግተዋል...የተዓምር ጥሩ እንጂ እንዴት ክፉ ይኖረዋል ግን ፈጣሪስ መልካሙን እንጂ እንዴት እነዲህ ያለ ነገር ያደርጋል?...ይሄኔ ነው የአባ ደምሴ ቃል ከራሱ ላይ ጥምጥሙን ጠምጥሞ የሚመጣባቸው...እግዚአብሄር ድሃን ማበልጠግ እንደሚያውቅ ሁሉ ባለጠጋን ማደህየትም እንዲሁ ያውቅበታል...ፈጣሪ እንዴት ችግር ይፈጥራል ታድያ?...ሃብታሙን ለማደህየት የሚያወጣውን ኃይል ምናለ አንዱን ድሃ ኃብታም ቢያደርግበት? እንደው ዝም ብሎ ኃይሉን

በረባ ባልረባው መጨረስ ምን የሚሉት ነው?...ሳያስቡት ከፈጣሪ ሙግት መጀመራቸው እንደክፉ ነጥብ ተቆጥሮ በድህነት እንዳይቀጡ በፍርሃት ይባሱን ልባቸው ራደ...ለዚህ አስተሳሰባቸው ፈጣሪ እመንበሩ ላይ ሆኖ "ምን ያህል ብትጠግቢ ነው ከእኔ የምትሚገኝ!!!" ብሎ ድህነትን ስያሰፍራባቸው ታያቸውና ዘገነናቸው...አሁንስ ቢሆን የትኛው ሃብታቸው ነው...ቢያንስ ምንም ሳይሰሩ ወር እየቆጠረ ብር የሚያመጣ የኪራይ ቤት አላቸው....እሱንስ ማን አየበት ተመስገን ነው ብለው እንዳያመሰግኑ የልኬለሽ ልክ አልባ ለቅሶ እፊታቸው ይደነቀራል...እንባ ገንዘብ ይሆን ይመስል መንታ መንታ እንባ የምታወርደው...

"እየጠበቅኩሽ እኮ ነው የማሩን አባባል በሌላ እለውጥልሻለሁ ብለሽ ዝም አልሽ" ፈገግ ብለው ያ የሃሳብ ባለጠጋ የሆነ መሬት በፈገግታ አዩት...መሬቱ ፈገግታቸው አሞቀው ይሁን የለጉትን ሃሳብ ወረወረ...

"ውሃም ሲበዛ ሽንት ይሆናል"

"እና ታድያ ውሃ ተጠጥቶ ምን ሊሆን ነው ድሮስ?"

"እህልም ሲበዛ ያቅራል እኮ" መለወጫውን ሰጡ

"የማያቅረው ስንት ሰው አለ ሆደ ስልቻ" ቁጣቸው ገነፈለ

ምነው ከእኔ በላይ እውቀት ለአሳር አልሽ...ማርም እኮ ሲበዛ..." ሳይጨርሱት ሳቅ አደናቀፋቸው

"ይሄን እድሜ ኖረን አልፈንበታል ፎንቸር ፎንቸር ኋላ መዘዙ ብዙ ነው"

"እኔ እኮ አንቺ እነደምታስቢኝ አይነት ሰው አይደለሁም የሚጎዳኝን እና የሚጠቅመኝን ለይቼ የማውቅ ሰው ነኝ"

"የሚጎዳሽን እነደማታውቂማ እያሳየሽኝ አይደለ"

"ቆይ አንቺ አትተማመኚብኝም ማለት ነው"

"እንዴት ልመንሽ እቱ አካልሽ ከቀን ቀን እንደአበባ ውበቱ እየፈነዳ ይወጣል...ወንዱ እንደው ከአዳም አንስቶ አእምሮ ብላሽ ሆኖ ነው የተፈጠረው ይሄን አካል አይቶ ስሜቱን የትኛው ወንድ ነው የሚያስታግስ ነገ እኮ ሆድሽን አሳብጠሽ ብትመጪ እኔን ምንም አትጎጂኝ

እንዲያውም አያት አድርገሽኝ በጊዜ ወግ ታሳይኛለሽ ሰው ስለሚያወራውም ግድ የለኝ ዲቃላ ታቀፈች ይበሉኝ እንዲህ መባል ብርቁ አይደለም አንቺንም ስወልድ እንዲህ ነው የተባልኩት..." ንግግራቸውን ለአፍታ ገታ አደረጉ ዓይናቸው ከአድማስ ባሻገር የሚያይ ይመስላል

"...እኔ የሚያሳስበኝ የአንቺ ህይወት ብቻ ነው፤ ደጅን የሚሆን ባል ቢኖርሽ በዛ ላይ ወንድ ልጅ ምንም ከሌለሽ መጫወቻ ነው የሚያደርግሽ ቢያንስ ተምረሽ ከቤት ወጣ ስትይ ነው በቅናት ከማን ውላ ይሆን እያለ ልቡ የሚሰቀለው፤ ወንዶች አላዋቂነታቸውን እንደምታውቅ ሴት የሚፈሩት ነገር የለም" ደመቀ እሳቸውን ትቶ የተማረች አገባ መባሉን መቼም ቢሆን ከአእምሯቸው የሚያወጡት ሃሳብ አይደለም

"ፍርሃትሽ እኮ ይገባኛል ግን የእኔና የዴቭ ግንኙነት አንቺ እንደምታስቢው አይደለም"

"ወንድና ሴት ተገናኝተው አኔ ካሰብኩት ውጭ ምን ያደርጉና ነው?"

"አይደለማ እኛ ሁሉንም ነገር በጊዜው ለማድረግ ቃል ተገባብተናል"

"እኮ ቃላችሁን እንዴት ልመን እንደጎመን አበባ የሚፈካ ውበትሽን እያየሁ እሱስ ከቃል ኪዳኑ ቢያፈነግጥ ይፈረድበታል እንዴ" የጎመን አበባ ደብዛዛ ወበት እንዳለው ዘንግተው ይሆን የልጃቸውን ውበት እንደጎመን አበባ ውበት ማመሳጠር ፈልገው እንደው እሳቸውም የገባቸው አይመስል

"አንቺ ደግሞ አካበድሽው" ያ ሃሳበኛ መሬት እጁን አውለብልቦ እንደጠራቸው ሁሉ አፈጠጡበት፤ አሁንም የሃሳብ ሸማ እየሸመነ ያለብሳቸው ጀመር...ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት...ቆንጂት ሻይ ልበልሻ ቡና ልበልሻ...ታስፈራ እንደሁ ብላ ፊቷን ታኮሳትራለች...ስትኮሳተሪ ውበትሽ እንደገጋነም አበባ ይበልጡን ይደምቃል...መኮሳተሯ ስለታወቀባት ይሆን ለፈገግታ ያደላ ገጽ ትለቅቃለች...ያን ፈገግታ ከሃሳብ ባህር ተቀድቶ የእውኑ አለም ገጻቸው ላይ ፈሰሰ...

"ምነው ፈገግ አልሽ?" ፈገግታቸው እንደነውር አስደነገጣቸው ፈገግ ያስባለኝ ይሄ ነው ብለው ቢናገሩት እና ትዝታቸውን በንግግር ነፍስ ቢዘሩበት ምንኛ በወደዱ ግን አይደለም ትዝታቸውን ነግረዋት እንዲሁም እሷ አክለፍልፏታል...

"ቆይ እሺ እሱን ስታውቂው ምን ያህል ጊዜሽ ነው" ትዝታቸውን መናገር አስጨንቋቸው የተናገሩት ነው፤ እንዲያው ይህን ርዕስ ለማዛወር ምን ብል ይሻል ይሆን ብለው

"አንቺ ደግሞ አሁን ብነግርሽ ጊዜው ስላጠረ በደንብ ምንነቱን አታውቂውም ልትይኝ ነዋ"

"አጭር ጊዜ ነው ማለት ነው?"

"ቆይ ለአንቺ አጭር ጊዜ ማለት ምን ያህል ጊዜ ነው?" ደመቀን አራት አመት ነበር ደጅ ያስጠኑት፤ ታድያ ጊዜ አብሮ ለመቆየት ጋሻ አያደለም እንዴ እንዴት ትቷቸው ሄደ? ምናልባት ብዙ ስላስጠበቁት ፍቅሩ ተገቢው ቦታ ሳይደርስ በጊዜ ብዛት አርጅቶ ከጥቅም ውጪ ሆኖ ይሆን...ፍቅር እና ገንፎ በትኩሱ ይባል የለ¡ ገንፎው ቀዝቅዞ ከሻገተ ኋላ ይሆን የደረሱበት!?...ጊዜ ሲረዝም ፍቅር ያጸና ይመስል ታድያ ለምን የጊዜውን ርዝመት መጠየቅ አስፈለጋቸው...የግብዝ ጥያቄ እንደጠየቁ ተሰማቸው

"አንቺ መናገሩ ምን አስፈራሽ እኔ የፈለግሁትን ልበል"

"አይደለማ"...የማይሰሙ ቃላቶችን አፏ ውስጥ ተጉመጠመጠች አልተፋችውም ዋጠቻቸው...ከዬቭ ጋር ፍቅረኛ መሆን ቶምቦላ እንደመቁረጥ ነው ቶምቦላ መቁረጥም ብቻ ሳይሆን በቶምቦላ መሸለምም ነው...ቶምቦላን እልፍ ቢመኘው እንደማያገኘው ሁሉ ዬቭንም ማግኘት እንዲሁ እድል ይጠይቃል በስንት ሴቶች ሲፈለግ አልገኝ ያለ ወንድ በራሱ ተነሳስቶ ፍቅሩን ከተናዘዘ እንዴት ወደኋላ ይባላል?...

"እማ ወንድ ልጅ እኮ ሴት ልጅን ትቶ የሚሄደው ሴት ልጅ አያያዙን ሳትችልበት ሲቀር ነው"...ብላ ብትናገር እናቷን ወንድ አያያዝ ስላልቻልሽበት ነው አባዬ ትቶሽ የሄድሽው ብሎ መሳለቅ ሆነባት...ዬቭን ከእሷ የሚያቆይ የሆነ ብልሃት እንዳላት ግን ይሰማታል፤እሱን ብትናገር የእናቷን ስጋት ታቀልል መስሎ ታያት ግን እንዴት አድርጋ ትናገረው...ቢናገሩ ትዕዝብት ባያወሩ አላዋቂነት! ምን ይሻላል እንደው!...